# ★ ዴሞክራሲያ ★

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ልሳን

ዴሞ ቅፅ 16 ቁ 3 ሐምሌ 1982


## ለመጪው ትውልድ አይለጉት ሀኬት!

የሀገር ወዳድ ስስ ብልቱ የሚገኘው በሀገር ሲመጡበት ነው። የሀገር ስም ሲጠራ ይነዝረዋል። የሚያመው ሁሉ አይሰማውም፤ የሚጉረበጠው አያመውም። መላ ሕዋሳቱ የተጠመዱበትን ሌላ ሌላውን ትተው ትኩረት ሰጥተው በተመሰጠ የሚያዳምጡት ሃገር የሚለውን ንዝረት ይሆናል።

ሀገር የአንድ ሕዝብ የሰብአናው፣ የክብር ኩራቱ፣ የወጉ፣ የባህሉ፣ ባጭር ቃልም የእሱነቱ ልዩ መገለጫው ስለሆነ ጉዳዮች ሲፈረዱ፣ ሲከብዱ ቢውሉ የሀገር ጉዳይ እያለ የመጀመሪያውን ረድፍ አይይዝም። ስለዚህም ባለ ሀገር ሆኖ ለመቆየት፣ ለቀጣይ ትውልዱም ለማስተላለፍ መራራ ትግል ይካሄዳል፤ ብዙ ተጋድሎ ይደረጋል። ለሀገር መሠዋት፣ መሞት የክብር ሞት፣ ሰማእትነት ስለሆነ በታሪክ ዓምደ ወርቅ ላይ ደረጃው ልዑል ነው።

ሀገርን በነፃነቷ ጠብቆ ለማቆየት ትውልድ ሲያልፍ፣ ትውልድ ሲተካ፣ ሁሉም በየተራው ከፍ ያለ መሥዋዕት እያቀረበ ክቡር ኩራትን፣ ነጻነትን፣ ጀግንነትን በታሪኩ ላይ እያተመ ያለፈው፣ ኩሩና ምሳሌነቱ ለዓለም ያንፀባረቀ የኢትዮጵያ ሕዝብም ያለው ጽኑ የሀገር ፍቅር ስሜት መንጊዜም የማይጠረጠር ነው።

የሕዝብን የሀገር ፍቅር ስሜት በመኮርኮር በዓለም ላይ በየጊዜው የተነሡ ፋሺስቶችና አምባገነኖች በአንድ ሀገር ውስጥ ነባራዊ ሁኔታዎች ይበስሉና የሚያስነሱትን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረ ሰብአዊ ችግሮችን ሠፊው ሕዝብ ራሱ በልታቸውን ለይቶ መፍትሔ እንዳይሰጣቸው የሀገሩም ባለቤት የሚሆንበትን አቅጣጫ እንዳይከተል

.../

ሀገራችን ከደረሰችበት የገደል አፋፍ ተራምዳ ትሸገር ዘንድ የመሸጋገሪያ መንግሥትን ድልድይ መዘርጋቱ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ እንደሆነ አብዛኛው በገጉድ ያየውና ያመነበት ይሁን እንጂ የዚያን ሀገር—አድን ድልድይ ንድፍ ዓምከራቢያዊ መሠረቱን ጥልቀት ሰጥቶ የሀገርን ክብደት እንዲችል በማድረጉ ረገድ ዓምሸራቢ የሚሰው ጽንሠ—ሐሣብ ላይ ያለው ግንዛቤ አራምባና ቆቦ አየረገጠ ገና ብዙ የሚቀረው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ታዲያም ይህንን ግንዛቤ ለማቀራረብና አንድ ፈርጅ ለማስያዝ የሚደረገው ጥረት አጥፍ ድርብ መጠመር ይኖርበታል፡፡

"ከወደቁ በኋላ መንፈራገጥ ለመመሳሰጥ" ይባላል፡፡ ወድቆ መነሣት ለሰው ልጅ የባህርይ ገንዘቡና የሰውነቱ አንዱ መመዘኛ ቢሆን እንደ አወዳደቁ ዓይነትና እንደደረሰበት ጉዳት መጠን ለመነሣት የሚያደርገው ትግል የተለያየ ክብደት ይኖረው እንጂ ቢያንስ ቀላል አይሆንም፡፡ በሕዝብ ደረጃ፣ በሀገር ደረጃ የሚመጣ ድቀት ደግሞ የርደት—መቃብርን ያህል ክብደት ያለው ስለሆነ ሕዝባዊ ገቢረ ተአምርን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ያ ብቃት ደግሞ ያለ ብዙ ገድልና ሰማእትነት የሚገኝ አይደለም፡፡ ባለመውደቅ ሚጥሮ መታገልን የመሰለ ቀላሉ ምርጫ ባለ እጅግ ከባዱን ምርጫ ከራባችን በላይ አባልፈን ለመጪ ትውልድ በመለጋት ይቅርታ የማይደረግለት ሀጢት በታሪክ ፊት እንዳንፈጽም ይህች ቅጽበት የያንዳንዱን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊን ቁርጠኛ ውሳኔ የምትጠይቅ የሞት ሰዓት መሆኗን የምር ማጤን ያስፈልጋል፡፡

የሕዝቦችና የአገር አንድነት በሕዝቡ ትግል
እውን ይሆናል !

እናቸንፋለን !